በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መዝገብ ቁጥር 238481

ህዳር 25 ቀን 2016 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

ሐብታሙ እርቅይሁን

አመልካች፡- 1ኛ. ወ/ሮ ማህሌት ተሾመ

2ኛ. ወ/ሮ ዘቢብ ተሾመ

3ኛ. ህፃን የአብስራ ተሾመ } ሞግዝት ወ/ሮ የአለምዘርፍ በላይነህ ቀርባል

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. ወ/ሮ ይመኙሻል ተስፋዬ አልቀረቡም

2ኛ. አቶ ታደለ ተስፋዬ ቀርቧል

3ኛ. አቶ ተገኝ ተስፋዬ አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ለነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ጉዳዩ የውርስ ንብረት ክርክር ሲሆን የክርክሩ አመጣጥ በአሟሙሩ ክሱ በቀረበበት በደቡብ ብሔሮች ፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ጋሞ ዞን ጨንቻ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ከሳሾች ፣ 1ኛ ተጠሪ ተከሳሽ አመልካቾች ደግሞ ጣልቃ ገብ ተከራካሪዎች ነበሩ፡፡ በጨንቻ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከሳሾች የነበሩት 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች አቅርበውት የነበረው ክስ የሟች አባታቸው አቶ ተስፋዬ መንግሻ ልጆች እና የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች መሆናቸውን ገልጸው የሥር ተከሳሽ የሉኑት1ኛ ተጠሪ የሟች ንብረት የሆነውን በጨንቻ ከተማ ቀበሌ 01 ውስጥ የሚገኘውን ቤት እና ሌሎች ንብረቶች ይዛ ስለምትገኝ ሟች ኑዛዜ ስላላተረፉ ውርስ አጣሪ ተሹሞ ድርሻቸው እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል፡፡ 1ኛ ተጠሪም ለክሱ በሰጡት መልስ ከሶሾች የጠየቁትን ቤትና ሌሎች ንብረቶች ሟች በህይወት እያለ በስጦታ የተላለፈላቸው መሆኑን በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡ የአሁን አመልካቾች በጣልቃገብነት ወደ ክርክሩ ገብተው ባቀረቡት አቤቱታ ሟች አባታቸው አቶ ተሾመ ተስፋዬ የሟቹ አቶ ተስፋዬ መንግሻ ሚስት የነበሩት የሟች ወ/ሮ ብዙነሽ መኩሪያ ልጅ ስለሆኑ ሟች አባታቸውን ተክተው ሟች አያታቸው ወ/ሮ ብዙነሽ መኩሪያ መሆናቸውን ገልጸው ለክርክር መነሻ የሆነው ቤትና ሌሎች ንብረቶች የሟች አያታቸው ወ/ሮ ብዙነሽ መኩርያ ጭምር በመሆኑ ውርስ አጣሪ ተሹሞ ድርሻቸው እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የውርስ አጣሪ በመሾም ውርሱ ተጣርቶ ሰኔ 24 ቀን 2013 ዓ.ም በቀረበው የውርስ አጣሪው ሪፖርት ላይ ግራ ቀኙ አስተያየት እንዲሰጡበት ያደረገ ሲሆን አመልካቾች ፣ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ንብረቶቹ የሚቾቹ አቶ ተስፋዬ መንግሻ እና ባለቤታቸው ወ/ሮ ብዙነሽ መኩሪያ መሆኑን ስከራካሩ 1ኛ ተጠሪ አከራካሪው ቤት ሟች አቶ ተስፋዬ መንግሻ በህይወት እያለ በስጦታ ውል ያስተላለፉላቸው መሆኑን ተከራካረዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም አከራካሪው ቤት ሟች አቶ ተስፋዬ መንግሻ በህይወት እያለ ለ1ኛ ተጠሪ በስጦታ የተላለፈ ነው ወይስ የሟች አቶ ተስፋዬ መንግሻ እና ሟች ባለቤታቸው ወ/ሮ ብዙነሽ መኩሪያ ያፈሩት የውርስ ሀብት ነው የሚል ጭብጥ ይዞ የግራ ቀኙን ምስክሮች ሰምቶ መዝገቡን እንደመረመረው፡- ሐምሌ 1 ቀን 2012 ዓ.ም ለጋሞ ዞን ፍትሕ መመሪያ ቀርቦ በተመዘገበ የሥጦታ ውል በክስ ማመልከቻው ላይ የተመለከተውን ቤት 1ኛ ተጠሪ በስጦታ ውል ያገኙ መሆኑን የሚያስረዳ ሲሆን የሥር ከሳሾችም ሆኑ ጣልቃ ገብ ተከራካሪዎች የነበሩት የአሁን አመልካቾች ውርስ አጣሪ ተሹሞ የውርስ ድርሻቸው እንዲሰጣቸው እንጅ የስጦታ ውሉ እንዲፈርስ የጠየቁት ጻኝነት ባለመኖሩ ሟች አቶ ተስፋዬ መንግሻ በሥጦታ ለ1ኛ ተጠሪ ያስተላለፉትን ቤት ልታካፍል አይገባም በማለት ስወስን ፣ በስጦታ ውሉ ለመተላለፋቸው ማስረጃ ያልቀረበባቸውን ሌሎች ንብረቶችን ለቀሪዎቹ ተከራካሪዎች ድርሻቸውን 1ኛ ተጠሪ እንደታካፍል ወስኗል፡፡ አመልካቾች ይህን ውሳኔ በመቃወም እንደቅደም ተከተላቸው ያቀረቡት የይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ በጋሞ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እና በደቡብ ብሔሮች ፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተቀባይነት ማጣቱ ለሰበር አቤቱታ መቅረብ ምክንያት ሆኗል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ለነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የአሁን ሰበር አቤቱታ የቀረበውም በየደረጃው ያሉ ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት በሰር ሰሚው ችሎት ለማሳረም ሆኖ የሰበር ቅሬታው ይዘት በአጭሩ፡- የሚች አቶ ተስፋዬ መንገሻ እና የሚች ወ/ሮ ብዙነሽ መኩሪያ የጋራ ንብረት የሆነውን ቤት የሚች ወ/ሮ ብዙነሽ ልጅ የሆነው ሚች አባታቸው አቶ ተሾመ ተስፋዬን ተክተው በውርስ ልያገኙ የሚገባውን ድርሻቸውን ጨምሮ ሚች አቶ ተስፋዬ መንገሻ ስጦታ ማድረግ እንደማይችሉ እየታወቀ እና አመልካቾች የስጦታ ውሉን ለመቃወም እድሜያቸው ያልደረሰ መሆኑን ጠቅሰው ተከራክረው እያለ የወረዳ ፍርድ ቤቱ የስጦታውን ህጋዊነት ሳይመረምር ውሉን በተደረግበት ጊዜ አልተቃወማችሁም በሚል አከራካሪውን ቤት ልታገኙ አይገባም በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል የሚል ነው፡፡

የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ ለ1ኛ ተጠሪ በሚች አባቷ አቶ ተስፋዬ መንገሻ ተደርጓል የተባለው የሥጦታ ውል በሚስት ድርሻ ጭምር የተደረገ መሆን አለመሆኑ ፤ የሚስት ድርሻ ሳይለይ የሥጦታ ተቀባይነት አግኝቶ በስጦታ ውሉ የተጠቀሰው ንብረት ሙሉ በሙሉ ለሥር ተከሳሽ የተወሰነበትን አግባብ ለመመርመር ሲባል የሰበር አቤቱታው ለሰበር ሰሚው ችሎት ይቅረብ ተብሎ ተጠሪዎች መልስ ሰጥተዋል፡፡

1ኛ መልስ ሰጪ መጋቢት 26 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት መልስ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ለሰበር አቤቱታው መሠረት የሆነው ውሳኔ ከተሰጠ ከአራት ወር በኋላ የቀረበ ጊዜ ያለፈበት መሆኑን ፤ አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት የጠየቁት ዳኝነት ውርስ አጣሪ ተሹሞ የውርስ ድርሻችን ይሰጠን የሚል ሆኖ በውርስ ሀብትነት እንዲጣራ የጠየቁት ቤት ለ1ኛ ተጠሪ በሕጋዊ የስጦታ ውል ተላልፎ የስጦታ ውሉም ውል ለመመዝገብ ሥልጣን ላለው አካል ቀርቦ የፀደቀ መሆኑንና የስጦታ ውሉ አስምልክቶ በሰበር ደረጃ የተነሳው ክርክር በስር ፍርድ ቤት ያልቀረበ አዲስ ክርክር መሆኑን ፤ የውርስ አጣሪ ባደረገው ማጣራት በሚች ስም ተመዝግቦ የሚገኘው 140 ካ.ሜ ቦታ እና ቤት ሚች ለ1ኛ ተጠሪ በስጦታ ማስተላለፋቸውን፣አመልካቾች ሚች በህይወት እያሉ ያደረጉትን ስጦታ ለማስለወጥ በሸማግሌ ጠይቀው ሚች ስጦታውን እንደማይለውጡ የነገሯቸው በመሆኑ ሚች ያድረጉትን ስጦታ የሚቃወሙ ከሆነ የስጦታ ውሉ እንዲፈርስ ክስ ማቅረብ ስገባቸው ስጦታውን አስመልክቶ ያቀረቡት ክርክር ሳይኖር ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት ስለሌው የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ልፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

2ኛ ተጠሪ በበኩላቸው ግንቦት 1 ቀን 2015 ዓ.ም በተጻፈ መልስ የሚች አቶ ተስፋዬ መንገሻ የመጀመሪያ ሚስት ወ/ሮ ሰንተሌ ደምሴ ድርሻ ሳይለይ የውርስ ሀብት ሊጠየቅ አይገባም፡፡ 1ኛ መልስ ሰጪ ልጅ ወይም ሚስት መሆናቸው ባልተረጋገጠበት የውርስ ሀብቱን መጠየቅ የሚያስችል መብት የላቸውም፡፡ ውርሱ በአግባቡ ተጣርቶ ንብረቱ የማን እንደሆነ ሳይለይ በደፈናው መወሰኑ አግባብ

አይደለም፡፡ የአመልካቾች አባት የሐነው ሚች አቶ ተሾመ ተስፋዬ የሚች አቶ ተስፋዬ መንገሻ ልጅ ስላልሆነ የሚች አቶ ተስፋዬ መንገሻን ውርስ መጠየቅ ስለማይችል የሚች ውርስ ለአመልካቾች ሆነ ለ1ኛ መልስ ሰጭ አይገባም ተብሎ የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እንዲሻር ጠይቀዋል፡፡ 3ኛ ተጠሪ መጥሪያ የደረሳቸው መሆኑ በቃለ መሀላ የተደገፈ አቤቱታ ቀርቦ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡

አመልካቾች ሚያዝያ 26 ቀን 2015 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ ሰበር አቤቱታቸውን ያቀረቡት የማስፈቀጃ አቤቱታ አቅርበው ተፈቅዶላቸው መሆኑና የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለ መልኩ የተመለከተዉ የግራ ቀኝ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ሲል የያዘዉን ጭብጥ እና በስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40 (2)ድንጋጌ መሠረት የግል ንብረት ማለት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ወይንም ንብረት የማፍራት መብት የተሰጣቸው ማህበራት በጉልበታቸው ፣ በመፍጠር ችሎታቸው ወይንም በካፒታላቸው ያፈሩት ንብረት መሆኑ ተደግጓል። በዚህ መልክ የተገኘ ባለሃብትነት በህግ ከተመለከቱት ሥርዓቶች ውጭ ልገደብ የማይችል የሕግ ጥበቃ የተደረገለት ሰፊ መብት እንደሆነ የፍትሐብሔ ሕግ ቁጥር 1204 ያስገነዝበናል። ባለሀብትነት በሕግ ወይንም ባለጉዳዮች በሚያደርጓቸው ሕጋዊያን ተግባሮች የሚተላለፍ ሲሆን የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች ባለሀብትነት ሲተላለፍ በማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ ማስመዝገብ አስፈላጊ መሆኑን የፍትሐብሔር ሕጉ ቁጥር 1184 እና 1185 ያስገነዝበናል። በዚህ መልክ ሀብትነቱ ለሌላ ሰው ስተላለፍ ሀብትነት ቀሪ እንደሚሆን ከፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 1189 ድንጋጌ መረዳት ይቻላል። የባለሀብትነት ምስክር ወረቀት የሚሰጠው በፍ/ሕ/ ሕግ ቁጥር 1553- 1636 ድንጋጌዎች መሠረት ነው። የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች በኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ ያላቸው ሚና ከፍተኛ በመሆኑ የባለሀብትነት መብቱ እና ሌሎች በነዚህ ንብረቶች ላይ መብትን የሚያቃቁሙ ሕጋዊያን ተግባሮች በጽሁፍ ሆኖ በማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ ላይ ሰፍሮ የነዚህ መብቶች መኖር በተለየ ማስረጃ እንድረጋገጥ መደረጉ ሕጉ ለነዚህ ንብረቶች የተለየ ጥበቃ እደሚያደርግ ማሳያ ነው። የባለሀብትነት ምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው የንብረቱ ባለሃብት እንደሆነ እንደምቆጠር ከፍ/ሕ/ሕግ ቁጥር 1195 ድንጋጌ መረዳት ይቻላል። የፍ/ሕ/ ሕግ ቁጥር 1195 የሕግ ግምት ሊስተባበል የሚችል ስሆን በፍ/ሕ/ ሕግ ቁጥር 1196 ሥር የተመለከቱት ሁኔታዎች መኖራቸዉን በማንኛውም ማስረጃ በማረጋገጥ ሊስተባበል ይችላል።

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ለነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የፍትሐ ብሔር ክርክር የሚመራው በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ መሆኑን የህጉ ቁጥር 1 ድንጋጌ ያመለክታል፡፡ የሥነ ሥርዓት ሕጉ ክስ ፣ የመከላከያ መልስ እና የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ የሚቀርብበትን ሥርዓት የዘረጋ ሲሆን ፍርድ ቤቶችም የቀረበላቸውን የፍትሐ ብሔር ክርክር የሥነ ሥርዓት ሕጉ በተዘረጋው አግባብ የመምራት ኃላፊነት አለባቸው፡፡

ውል የሚቋቋው በሕግ አግባብ ሆኖ በሕጉ የተመለከቱ መለኪያዎች አለመሟላት ውሉን አንድም ፈራሽ (voidable) አልያም ከነአካቴው ዋጋ አልባ (void) ሊያደርገው ይችላል፡፡ በፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 1808(1) ሥር የተመለከቱት ግድፈቶች ውሉን ፈራሽ (voidable) የሚያደርጉ ሲሆን ፣ በቁጥር 1808(2) ከተመለከቱት ግድፈቶች ውስጥ ውሉ የተደረገበት ጉዳይ ወይንም ምክንያት ከህግ ውጭ ከሆነ ፣ ወይንም ሕልናን የሚቃረን ሲሆን ውሉን ዋጋ አልባ (void) ሊያደርገው እንደምችል ከድንጋጌው ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ የጭንቻ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከሳሾች የነበሩት 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ያቀረቡት ክስ የሚች አባታቸው አቶ ተስፋዬ መንገሻ ልጆች እና የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች መሆናቸውን ገልጸው የሥር ተከሳሽ የሑኑት1ኛ ተጠሪ የሚች ንብረት የሆነውን በጨንቻ ከተማ ቀበሌ 01 ውስጥ የሚገኘው ቤት እና ሌሎች በ1ኛ ተጠሪ ተይዞ የሚገኙ ንብረቶች ውርስ አጣሪ ተሹሞ ድርሻቸው እንዲወሰንላቸው የጠየቁ ሲሆን በጣልቃገብነት ወደ ክርክሩ የገቡት አመልካቾች ሚች አባታቸው አቶ ተሾመ ተስፋዬ የሚቹ አቶ ተስፋዬ መንገሻ ሚስት የነበሩት የሚች ወ/ሮ ብዙነሽ መኩሪያ ልጅ ስለሆኑ ሚች አባታቸውን ተክተው ሚች አያታቸው ወ/ሮ ብዙነሽ መኩሪያ ባለቤታቸው ከነበሩት ሚች አቶ ተስፋዬ መንገሻ ጋር ያፈሩትን ለክርክር መነሻ የሆነው ቤትና ሌሎች ንብረቶች የሚች አያታቸው ወ/ሮ ብዙነሽ መኩሪያ ድርሻ ውርስ አጣሪ ተሹሞ ድርሻቸው እንዲወሰንላቸው ላቀረቡት አቤቱታ 1ኛ ተጠሪ በሰጡት መልስ ንብረቶቹ ከሚች አቶ ተስፋዬ መንገሻ በስጦታ ያገኙ መሆኑን ተከራክረዋል፡፡

በፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 944 እና 956 መሠረት የውርስ ማጣራት ተግባር ዋና ዓላማው በፍትሐ ብሔር ሕጉ 826(2) እና በሌሎች የውርስ ህግ ድንጋጌዎች መሰረት ለወራሾች በውርስ ሊተላለፍ የሚችለው በሕግ ጥበቃ የተደረገለት የአውራሹ የሐኑ የንብረት መብት መኖሩን ለማረጋገጥ ነው፡፡ 1ኛተጠሪ አመልካቾች የሚቹ አቶ ተስፋዬ መንገሻ ሚስት የነበሩት የሚች ወ/ሮ ብዙነሽ መኩሪያ የአከራካሪው ቤት ግማሽ ባለድርሻ መሆናቸውንና አመልካቾች ሚች አባታቸውን ተክተው ሚች አያታቸው ወ/ሮ ብዙነሽ መኩሪያ ወራሾች ነን በማለት ያቀረቡት ክርክርን ሳይቃወሙ ቤቱ በስጦታ ተላልፎልኛል በማለት ስለሚከራከሩ አከራካሪው ቤት የማነው? የአከራካሪውን ቤት ባለሀብትነት ለማስተላለፍ ተደርጓል የተባለው ሕጋዊ ተግባር (የስጦታ ውሉ) በህግ ጥበቃ ሊደረግለት የሚችል የንብረት መብት ለ1ኛ ተጠሪ ማስተላለፍ አለማስተላለፉ ወይንም አከራካሪው ቤት የውርስ ሀብት ሆኖ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ለነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በፍትሐ ብሔር ሕጉ አንቀጽ 826(2) መሠረት ለወራሾች ሊተላለፍ የሚችል መሆኑ አልያም በሕግ ተቀባይነት ባለው የስጦታ ውል በፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 1184 እና 1185 መሠረት ለ1ኛ ተጠሪ ተላልፎ በፍትሐብሔ ሕግ ቁጥር 1204 ባለሀብት የሆኑበት የግል ንብረት መሆን አለመሆኑ በተነሳው የክርክር አውድ ውስጥ ታይቶ ውሳኔ ልያገኝ የሚችል ነው፡፡

ሲጠቃለል ለክራክሩ ምክንያት የሉነው በጨንቻ ከተማ ቀበሌ 01 ውስጥ የሚገኘውን ቤት የሚች ወ/ሮ ብዙነሽ መኩሪያ እና ሚች አቶ ተስፋዬ መንገሻ የባልና ሚስት ንብረት በመሆኑ የሚች ወ/ሮ ብዙነሽ መኩሪያ ድርሻ በውርስ ልተላለፍልን ይገባል በማለት አመልካቾች ላቀረቡት አቤቱታ 1ኛ ተጠሪ በሚች አቶ ተስፋዬ መንገሻ በተደረገ የሥጦታ ውል ተላልፎልኛል በማለት ስለተከራከሩ የፀና የስጦታ ውል ቢኖርም የውል ይፍረስልኝ ዳኝነት አልቀረበም በሚል የውሉ ሕጋዊነት ተመርምሮ አከራካሪው ቤት ለ1ኛ ተጠሪ በሥጦታ የተላለፈ ነው ወይስ የውርስ ሀብት በመሆኑ ለአመልካቾች ሊተላለፍ የሚችል የውርስ ድርሻ መኖር አለመኖሩ መጣራት ሲገባው የውል ይፍረስ ዳኝነት አልቀረበም በሚል አመልካቾች ያቀረቡት በአከራካሪው ቤት ውርስ ድርሻ ክስ ውድቅ መሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስለተገኘ ቀጣዩ ተወስኗል፡፡

ዉሳኔ

1. በደቡብ ብሔሮች ፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚው ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 38994 ነሃሴ 06 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠው ውሳኔ እና ትዕዛዝ ፣ የጋሞ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር 42646 ህዳር 12 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠው ውሳኔ እና ትዕዛዝ ፣ እንዲሁም የጨንቻ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር 00479 ጥቅምት 11 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ ፣ ውሳኔ እና ትዕዛዝ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ - ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 9(1/ለ) መሠረት **ተሽሯል**፡፡

2. የጨንቻ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በፍርድ የዘጋውን የመዝገብ ቁጥር 00479 አንቀሳቅሶ አከራካሪው ቤት የማነው? የአከራካሪውን ቤት ባለሀብትነት ለማስተላለፍ ተደርጓል የተባለው ሕጋዊ ተግባር (የስጦታ ውሉ) በህግ ጥበቃ ልደረግለት የሚችል የንብረት መብት ለ1ኛ ተጠሪ ማስተላለፍ አለማስተላለፉ ወይንም አከራካሪው ቤት የውርስ ሀብት ሆኖ በፍትሐ ብሔር

ሕጉ አንቀጽ 826(2) መሠረት ለወራሾች ሊተላለፍ የሚችል መሆኑ አልያም በሕግ ተቀባይነት ባለው የስጦታ ውል በፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 1184 እና 1185 መሠረት ለ1ኛ ተጠሪ ተላልፎ በፍትሐብሔ ሕግ ቁጥር 1204 ባለሀብት የሆኑበት የግል ንብረት መሆን አለመሆኑ አጣርቶ ሕጋዊ ውሳኔ እንዲሰጥ መዝገቡ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ - ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 9(2) መሠረት ተመልሶለታል፡፡

3. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ውሳኔ አግኝቶ ስለተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሃሳብ ልዩነት

ስሜ በተራ ቁጥር አምስት ላይ የተሰየምኩት ዳኛ ከአብላጫው ሃሳብ የተለየሁበትን ምክንያት እንደሚከተለው አስፍሬያለሁ፡፡

ክርክሩን በፍትሐብሄር ስነ ስርዓት ህጉ መሰረት መምራት እና መቆጣጠር የፍርድ ቤቱ ኃላፊነት ሲሆን በተገቢው ሁኔታ ካልተመራ የስነ ስርዓት ህጉን ዓላማዎች የሆኑትን እንደ አንጻራዊ እውነትን የመፈለግ ስነ ስርዓታዊ ፍትህ ክርክርን ውጤታማ ወጭና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ አግባብ መምራት የመሳሳሉትን ማሳካት ስለማይቻል የተከራካሪዎችን መብት ይነካል፡፡ ክርክር የሚወሰነው በተጠየቀው ዳኝነት አግባብ እንደሆነ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ182(2) ላይ ተመልክቷል፡፡ ፍርድ ቤቱም ከቀረበው ዳኝነት አኳያ ከግራ ቀኙ ክርክር በመነሳት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ246 እና ተከታዮቹ መሰረት በተነሱት ጉዳዮች ሰጭብጥ መስርቶ ውሳኔ የመስጠት ኃላፊነት አለበት፡፡ ፍርድ ቤት ስለጉዳዩ አጣርቶ በመወሰን

የተከራካሪዎች የመደመጥ መብት ማክበርና የፍትህብሄር ስነ ስርዓት ህጉን እውነት የመፈለግ ዓላማ የማሳካት ኃላፊነጽ አለበት፡፡ ተከራካሪ ወገን በአግባቡ የተሰማ ማስረጃው በአግባቡ ግምት ውስጥ የገባና ፍርድ ቤቱ ህጉን እና የቀረበውን ማስረጃ መሰረት አድርጎ የወሰነው ስለመሆኑ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ ክርክሩን በማስረጃ ሳያጣሩ መወሰንም ፍርድ ቤት በህግ የተጣለበትን ክርክርን የመምራት ኃላፊነት አለመወጣት ነው፡፡

ከክርክሩ እንደተገነዘብኩት ክርክሩ የውርስ ሀብት ይጣራልኝ አቤቱታን የሚመለከት ሲሆን 1ኛ ተጠሪ የውርስ ሀብት ተብሎ እንዲጣራ የተጠየቀው ቤት 01/11/2012ዓ.ም በፍትሐ መምሪያ በኩል በተረጋገጠ የስጦታ ውል የተላለፈልኝ ህጋዊ ንብረቴ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ የክስ አቤቱታው የውርስ ሀብት እንዲጣራ የቀረበ ዳኝነት እንጂ ውል እንዲፈርስ የተጠየቀ ዳኝነት አይደለም፡፡ በውርስ ሀብት ማጣራት ሂደት ንብረቱ የሟች የውርሰ ሀብት አለመሆኑ ላይ ክርክር ከቀረበ ፍርድ ቤቱ ንብረቱ የውርስ ሀብት መሆን አለመሆኑን የማጣራት ኃላፊነት አለበት ንብረቱ በውል ለ3ኛ ወገን የተላለፈ ነው በሚል ክርክር ከቀረበም ውሉ በህግ አግባብ መብትና ግዴታ ሊያስተላልፍ የሚችል ውል በማቅረብ መብቱን ማሳየት የቻለ ተከራካሪ ካለ በውርስ ማጣራት ሂደት ውሉ ሊፈርስ የሚገባው መሆን አለመሆኑ በቅድጥነት ተይዞ ሊወሰን አይችልም ንብረቱ በውል ከተላለፈ የውርስ ሀብት ስለመሆኑ ማስረጃ ባለመቅረቡ ከውርስ ሀብት ማጣራት ዝርዝር ውስጥ ማስወጣት ይኖርበታል ንብረቱ የተላለፈበት መንገድን በፍ/ህ/ቁ1808 አግባብ መሰረት ህጋዊ ውጤት የለውም ተብሎ ውሉ እንዲፈርስ ዳኝነት መጠየቅ የፈለገ ወራሽ ክስና ግልጽ ዳኝነት ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት በማቅረብ መብቱን ከሚያስከብር ባለፈ በውርስ ማጣራት ፋይል የውል ይፍረስልኝ ዳኝነት አብሮ ሊወሰን አይችልም በዚህ ረገድ የስር ፍርድ ቤቶች የውል ይፍረስ ክርክር በውርስ ሀብት ማጣራት ክርክር ሊታይ አይገባም በማለት የደረሱበት መደምደምያ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ባለመሆኑ ውሳኔው ሊፀና ይገባ ነበር በማለት በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

ፋ/ዘ

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ለነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !